# ይድረስ ለአምባሳደር ዲበኩሉ

## ከአራዳ ልጆች

መልዕክተ- አራዳ
አቅራቢ:- መስፍን ማሞ ተሰማ
msfntessema@yahoo.com.au

**ይድረስ ለአምባሳደር ዲበኩሉ!**

*ተቀማጭነቱ ፈረንጅ ሀገር። አድራሻው ያልታወቀ። ወኪልነቱ ለጦቢያ።*

ወዳጃችን ዲበ! ሹመት ያዳብርህ! እንዳንልህ ሹመትህ አልፀደቀም። ቅፅበታዊ ደስታ ደምህን አሟሙቆት ከሆነም ቀዝቃዛ የሎሚ ጭማቂ ጋብዘንሃል። ገዝተህ ጠጣበት። እ ነሆ  የአሿሿምህና አሻሻርህ ዝርዝር እንዲህ ነበር...

<u>ማመልከቻ</u>
ለአራዳ ልጆች ጉባኤ
አመልካቾች የዲበኩሉ ወዳጆች

ጉዳዩ፡- ለወዳጃችን ዲበ ሊቁ ልቅልቁ የአምባሳደርነት ሹመት እንዲሰጥልን። ምክንያታችን-

1. የባህር ማዶ ወገኖቻችንን ከጦቢያ ጋር ያገናኘ ወይም የኛን ለባህር ማዶ፤ የባህር ማዶውን ለኛ የሚያቀባብል ጉዳይ ፈፃሚ (ነገረ ፈጅም ሊባል ይችላል) በመሆኑ፤

2. ሀገር ናፋቂ፤ ወገን አካባሪ፤ ለወገን ተቆርቋሪ፤ እኛን ጠያቂ በመሆኑ፤

3. ከላይ ያስቀመጥናቸው ቱባ ቱባ ገድሎች የአምባሳደርነት ሹመት (ዛሬ በሀገር ላይ የዘመተ ባንዳ ሁሉ የህዝብን ድምፅ ማጅራት በመታ አምባገነን መንግስት ለሚሾመው) ቢያንሰው እንጂ የማይበዛበት በመሆኑ፤ ሹመቱ ቢሰጠው ደግሞ ለበለጡ ሀገራዊና ወገናዊ ገድሎች የሚያነቃቃው መሆኑ፤

ከነዚህ ምክንያቶች ተነስተን ከግንቦቱ የምርጫ ድራማ በኋላ አራት ኪሎ ቤተመንግስት አፍንጫ ስር የተሰየመው የአራዳ ልጆች ጉባኤ ማመልከቻችንን መርምሮ ወዳጃችን ዲበኩሉን በሚኖርበት ፈረንጅ ሀገር በአምባሳደርነት እንዲሾምልን በትህትና ስንጠይቅ ጉባዔው ለሚያሳልፈው ማንኛውም ውሳኔ ተገዥዎች መሆናችንን ከአክብሮት ጋር እንገልጣለን።

ሹመት ለዲበኩሉ ጠያቂዎች

*********************

**ወዳጃችን ዲበ!** ይህ አጃኢበኛ የሆነ የሹመት መጠየቂያ ማመልከቻ አራት ኪሎ ቤተመንግስት አፍንጫ ስር የተገኘነውን የጉባኤውን እድምተኞች በሙሉ አስደምሞናል። የተሟሟቀና የጦፈ ውይይትም አስነስቷል።

"ሹመቱና ስሙ ይስማማሉ። አምባሳደር ዲበኩሉ። ግን ታዲያ አሁን ዲበን ብንሾመው መቸኮል አይሆንብንም?! ባህር ማዶ ባሉት ወገኖቻችንም ትዝብት ውስጥ እንዳንገባ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።" አሉ እማማ ድንቡሎ - ፈረንጅ አምላኩንና ኒቂሴን በፈረቃ እያዩ።

"ሹመቱና ስሙ ይስማማሉ ላሉት መቼስ ሹመት የማይስማማው ስም የለም። ለምሳሌ - አስመጪና ላኪ ሚኒስትር ዘበርጋ - ተብዪ ብሾም ከስሜ ጋር ልክክ የሚል ሹመት ነው። ወይም - የሀገር ውስጥ ንግድ ሚኒስትር ሽኩር - ቢባል ለሽኩር ነፍስ የሆነ ከስሙ የሚስማማ ሹመት ነው..." ዘበርጋ ንግግሩን ሳይጨርስ ጀማው በሳቅ ተናጋ።

"የተከበሩ ሚኒስትር ዘበርጋ! ሹመት'ኮ ጨው መጠቅለያ ወረቀት አይደለም።" ፈረንጅ አምላኩ ነበር።

"አንተ መቼስ ሽቃባ የሆንክ ነጃሳ ነህ።" አለ ሽኩር በላብ የወየበች የሌኒን ኮፍያውን ባዶ አናቱ ላይ እያሻሸ። ቀጠለና "አሁን ሀገሪቱ ላይ ካሉት የንግድ ሚኒስትሮች አንድ ዘበርጋ ወንድማችን ብዙ ነገር መስራት አይችልምና ነው?"

ፈገግ አለ ዘበርጋ።

“የንግድ ሚኒስትሮቹ ብዙ ናቸው እንዴ?” ጠየቀ ዋቅጅራ በሰፌድ እጁ ዘግኖ የቃመውን አሹቅ በቡና እያወራረደ።

“ምን ጥያቄ አለው? ሀገሪቱ በሞላ የምትመራው በንግድ ሚኒስትሮች አይደለም እንዴ?” ድንብላል ነበረች <ዱብ እዳ> የጣለችው። ሁላችንም ባርምሞ ተመለከትናት። በግርምት። እትዬ አቻምየለሽ ግን ያቺን ምስጢራዊ ፈገግታቸውን ፈገግ ሲሉ አ ስተዋልን።

“ጉዳዩን ብታብጥሪልን?” ጠየቀ ዋቆ።

“ማበጠርም ማንቀርቀብም አያስፈልገውም። ሀገር ያወቀው፤ ፀሀይ የሞቀው እውነት ነው። ይህቺ ሀገር መንግስት የላትም። ያሏት የንግድ ሚኒስትሮች ናቸው። ይነግዱባታል። ያተርፉባታል። ትርፉን በግል ካዝናዎቻቸው ከሀገር ውጪ ይቆልፉበታል።

“ለውጪ መንግስታት ልዩ ልዩ የማእረግ ስማቸውን ያስተዋውቃሉ። ሀገርን በማስተዳደር በኩል ግን ሁሉም ነጋዴዎች ናቸው። በሀገር ንብረትና ሀብት የካበቱ።

“ከአራት ኪሎ ቤተመንግስት ቁንጮዎች እስከ ጭፍሮቻቸው የሀገሪቱን ሀብትና ንብረት በማጋበስ ላይ ያልዘመተ ማን አለ? **እድገት ማለት ምንድን ነው? በህብረት መዝረፍና ማዘረፍ?** የዘራፊ ሀብታሞችን መፍጠር? እድገት ማለት ምንድን ነው? ህንፃ መገንባት? ለዛውስ ቢሆን ህንፃዎቹ የነማን ናቸው? ከአስር ህንፃ ስምንቱ የንግድ ሚኒስተሮቹ አይደሉምን?

“በየመገናኛ ብዙሃን እድገት አመጣን ይሉናል፤ እድገቱ ምኑ ላይ ነው? አልፎ አልፎ አስፋልት መዘርጋት? **ጣልያንም እኮ ስንትና ስንት አስፋልትና ድልድይ ሲዘረጋ ነበር**። ለኢትዮጵያ እድገትና ለኢትዮጵያ ህዝብ በማሰብ ነበር? አልነበረም። ጦቢያን እየተዘዋወረ ረግጦ ለመጋዛት! እሳት ካየው ምን ለየው?!

“ሀገራችን አቁማዳ ይዛ ርጥባን በመለመን በዚህ ዘመን ባሰባት እንጂ አልቀለላትም። ይህ እድገት ነው? የቀድሞው መንግስት ምፅዋት ሲለምን ቤሳ የሚሰጠው የውጪ መንግስት አልነበረም። ይህ የንግድ ሚኒስትሮቹ መንግስት ግን አለማመኑን ተክኖበታል። ተራቆበታል። ዲሞክራሲ....ነፃ ምርጫ...አልቃይዳ...ሶማሊያ...ሁትሲ....ቱትሲ... ይላቸዋል፤ መፅዋቾቹን ምእርባዊያን መንግስታትን። የሽቀጦቹን አይነት ይዘረዝርላቸዋል፤ ለኢንግሊዝ እና ለአሜሪካን። በሸቀጥ አመራረጥና አቀራረብ የተካኑ የንግድ ሚኒስትሮች ናቸዋ! በናንተው መጀን! ይላሉ እንግሊዝና አሜሪካን! ብርክ ይይዛቸዋል የሸቀጦችን አይነት ዝርዝር ሲመለከቱ።

“እና ይጎርፋል ገንዘቡ፤ ከመፅዋቾቹ። የት ነው የሚገባው? እርዳታውን ለጉድ ይልካሉ፤ ምን ዋጠው? ኤድስን ለመከላከል፤ በበሽታው የተለከፉትንም ለመታደግ ተብሎ ወደዚህች ሀገር የገባው ቁጥር ስፍር የሌለው መድሃኒትና ገንዘብ የት ደረሰ? ስንት መቶ ሺህ ምናልባትም ሚሊዮናት ህፃናት ናቸው ዛሬ በመላው ሀገሪቱ የበሽታው ተሸካሚ ሆነው በወላጅ አልባነት መንገድ ዳር የሚያድሩት?

“በየቤተክርስቲያኑ ታዛ የሚገኙት ህፃናት እድሜ ከአራትና ከአምስት አመት እድሜ ጀምሮ አይደለምን? የዚህች ሀገር ወጣት ትውልድ የነገው እጣ ፈንታ ምን ይመስላል? ዙሪያው ጨለማ!

“እኮ እንደምን ያለ መንግስት ነው በዜጎቹ ፍዳ እና ሰቆቃ - በየቴሌቪዥኑና በየሬዲዮው <እድገት አመጣን> እያለ የሚሳለቀው? ከየትኛውም ዘመን በላይ የእለት ኑሮ ከብዶን፤ በድህነት ወለል ተኝተን እየማቀቅን፤ በበሽታዎች እያለቅን፤ በገዛ ሀገራችን ካንዱ ክልል ሌላው ክልል እየተባለ፤ ባይተዋርና ባእድ እየተባልን፤... ምን አይነት <እድገት> ነው አመጣንላችሁ የሚሉን? **መከራችንና ፍዳችን የሚያበቃውስ መቼ ነው?**” ድንብላል ጣያቄዋን አንጠልጥላ ሀዘን በተላበሰ ገፅታ ጀማውን መቃኘት ጀመረች ...

“ቀን እስኪያልፍ ያለፋል። **ሲነጋ ሲል ይጨልማል።**” አሉ እትዬ አቻምየለሽ ከሩቅ የሚሰማ በሚመስል ድምፅ። ድንብላል ትንፋሿን ሰበሰበች። እትዬ አቻሜ ይቀጥሉ እንደሁ ጠበቀች። ምን እሷ ብቻ? እኛም እንጂ! የእትዬ አቻሜ ንግግር አይጠገብም። ግን አቻሜ አልቀጠሉም። ድንብላል ካቆመችበት ቀጠለች...

“በእድሜያችን አይተንም ሰምተንም የማንውቀው ከህፃን እስከ አዋቂ ለማኝ የሆነበት ዘመን ውስጥ አይደለም የምንገኘው? የእድገት መለኪያው ይህ ነው? እድገት ማለት ሀገራዊ ድህነት ነው? ኢኮኖሚው አደገ ይሉናል። **በጆርጅ ኦርዌል <አኒማል ፋርም>** መፅሀፍ ላይ <ከእኔ በላይ መሪ፤ ከእኔ በላይ አዋቂ ለአሳር> እንደሚለው አምባገነኑ የእንስሳቱ መሪ አሳማው ናፖሊዮን እና የእሱ ቢጤ አፈቀላጤው ስኩለር በረሀብ፤ በድህነትና በበሽታ ለሚማቅቁት የ<ፋርሙ> እንስሳት በየጊዜው እንደሚያቀርቡት የአሃዝ ድርድር አይነት የኢኮኖሚ እድገት! ሃያ አመት ሙሉ ድህነትን መቅረፍ ያልቻለ የኢኮኖሚ እድገት - እድገቱ ምኑ ላይ ነው?!

“ከከተማ እስከ ገጠር ወጣቱ ትውልድ ተስፋ በቆረጠ የህይወት ፅልመት ውስጥ አ ይደለምን?! ተምሮ ስራ ማጣት፤ የተማረው ከስራው መባረር፤ ጉቦኝነት፤ ዘረኝነት፤ በዜግነት መዋረድ፤ በታሪካችን መዋረድ፤ ያለ ፍትህ ወህኒ መማቀቅ፤ ወዘተ...ወዘተ  የሃያ አመት አገዛዝ መለያችን አይደሉምን? እድገት ማለት ይህ ነውን? አዎ! **ለዚህች ሀገር የሚሰራላት የለም! የሚነግዱባትና የሚከብሩባት ግን ብዙ ናቸው። አዎ! የዚህች ሀገር ሹማምንቶች በሙሉ ነጋዴዎች ናቸው። የንግድ ሚኒስትሮች መንግስት!!** . . . ዘበርጋ ከእነሱ አስር እጅ የተሻለ ይሰራል።” በረጅሙ ተነፈሰች፤ ድንብላል። ዘበርጋን አየችው። ፊቱ ሁሉ ጥርስ ሆኗል።

ድንብላል ብዙ አትናገርም። ብዙ ታዳምጣለች። ብዙ ታነባለች። ንግግሯ ምጥን ነው። ስትናገር የተከሸነ ስነ ፅሁፍ የምታነብ ትመስላለች።

“አንቺ ብቻ እናትሽ ወለድኩ ይበሉ፤ ድንብላሊ! አሁን አንጀቲ ቅቤ አጠጣሽው” አለ ዘበርጋ በምናውቃት ዜማ። የተለመደችዋን <ን>  ፊደል ድራሿን እያጠፋ። ፈረንጅ አ ምላኩን የጎሪጥ እየተመለከተ።

“ወንድም ዘበርጋ! ቅቤም ሆነ ሹመት እንዳማሩህ ይቅሩ” አለ ፈረንጅ አምላኩ፤ በተራው በፌዝ ፈገግታ ዘበርጋን እየተመለከተ። ሳቅና ቁም ነገር ሆነ።

“እኛስ ሹመቱ ቀርቶብን በሀገራችን እንደ ጥንቱ በነፃነት እየተዘዋወርን ነግደንና ሰርተን መኖር በቻልን!” አለ ሽኩር ጥልቅ ሀዘን ባዘለ የሚርገበገብ ድምፅ።

ዝምታ። እንደ መቃብር የከበደ ዝምታ።

ትንሽ ቆይቶ፤

“ቅቤውም ቢሆን ከምድረ ኢትዮጵያ ጠፍቶ አይደለም። ቡና እና ቅቤውን የግላቸው ያደረጉት አልጠግብ ባይ አሳማዎች ሀገሪቷን እንደ መዥገር ተጣብቀውባት እንጂ!” ከዝምታው በኋላ ቁጭት በተላበሰ የረጋ አንደበት ዋቅጅራ ነበር የተናገረው፤ የፈረንጅ አምላኩን ተረብ በመቃወም።

ሌላ ዝምታ። ሁላችንም በዚህች ባልታደለች፤ መከራዋን ከዘመን ዘመን መቅረፍ ባልተቻለው ሀገራችን ላይ እየደረሰ ባለው ግፍና ምዝበራ ግዝፈትና ውስብስብነት የ ሀሳብ ባህር ውስጥ ሰጠምን . . .

“በፍርድ ቀን ሁሉም እንደ ስራው ይፈረድበታል። የግፍ እንባ ጎርፍ ሆኖ ግፈኞችን የሚያጥለቀልቅበት ጊዜ ቀርቧል። ውስጥ ለውስጥ የሚጋጋመው የተዳፈነው እሳት እሳተ - ገሞራ ሆኖ የሚፈነዳበት ጊዜ ደርሷል። . . . ብፁፅ አባታችን **አባ ዠንበሩ** እንዳስተማሩት. . . **ሊነጋ ሲል ይጨልማል።** ይህ ወጣት ትውልድ የብሩህ ዘመን ማብሰሪያ፤ የኢትዮጵያን ትንሳኤ ማረጋገጫ ደመራ ይለኩሳል። በደመራው ሀያል ብርሀንም ጨለማው ይገፈፋል!” አለች ኒቂሴ፤ እምነትና ተስፋ ባዘለ አንደበት።

ሌላ ዝምታ።

“ልጆቼ!” አሉ እትዬ አቻምየለሽ “ ልጆቼ፤ ሁሉም በጊዜ ይሆናል። ለሁሉም ጊዜ አለው - አይደል መጥሐፉስ  የሚለው? እና ነገ ሌላ ቀን ነው። ለማንኛውም አሁን ወደ ጀመርነው ጉዳይ እንግባ። የማመልከቻው ነገር እኮ ተረሳ።” አሉን ከፈገግታ ጋር። እናም ከየጠለቅንበት የሀሳብ ማእበል ተመንጥቀን ወጣን። እነሆ ዲበኩሉን በ አንባሳደርነት እንድንሾም በቀረበልን ማመልከቻ ላይ በአንድ ድምጥ የሚከተለውን ወስነናል።

**ውሳኔ**

ወዳጃችን ዲበኩሉ በሚኖርበት የፈረንጅ ሀገር ለጦቢያና ለወገን የሚጠቅምና የጠቀመ የዲፕሎማሲ ስራ ለመስራቱ ወይም እየሰራ ለመሆኑ አንዳችም ፍንጭ የለም። ማመልከቻውም የተጨበጠ መረጃ አላቀረበም።

አምባሳደርነት ሀገራዊ ተልእኮ ነው። ከባድ ሃላፊነት። ይህንን ሀገራዊና ወገናዊ ሃላፊነት ለመቀበል ዲበኩሉ ምን ፈየደ? ብቃቱስ?

የጦቢያን ሰቆቃና ምዝበራ፤ የህዝቦቿን የነፃነትና የፍትህ እጦት በሚኖርበት ሀገር የ መንግስት ሀላፊዎች መካከል ልዩ ልዩ መድረኮችን ተጠቅሞ ምን የፈየደው ሀገራዊና ወገናዊ ተጨባጭ ተልእኮ አለ?

ምን ያህል ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶችን ያለመታከት አድርጓል? በማድረግስ ላይ ይገኛል? ለአራት ኪሎዎቹ አምባገነኖች ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ድጋፍ በመስጠት ምርኩዝ ለሆኑዋቸው መንግስታት ሀቅን አሳውቆ፤ እውነቱን አጥርቶ በማሳየት - ምን ያህል ለፍትህና ለነፃነት ድምፃችውን እንዲያሰሙ፤ ከድጋፋቸውም እንዲቆጠቡ ማድረግ ችሏል? ዲበ ይህንን ለማድረጉ ወይም በማድረግ ላይ ለመሆኑ ማረጋገጫ በሌለበት እንደምን የአምባሳደርነት ሹመት ሊሰጠው ይችላል?

ዲፕሎማሲያዊ ተልእኮ ደግሞ ሀገርንና ወገንን ያሉ ከባህር ማዶ የሚኖሩ ወገኖቻችን ሁሉ የኢትዮጵአዊነት ሃላፊነታቸው - የእምነት እዳ ግዴታቸው ነው። ያም ሆኖ ይህንን የኢትዮጵያዊነት እምነት እዳ ሃላፊነት እየተወጡ ለሚገኙት በሙሉ የአምባሳደርነት ሹመት እንሰጣቸዋለን ማለትም አይደለም።

ለነፃነትና ለፍትህ ወገኑንና ሀገሩን የመርዳት ግዴታ በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምን ዜጋሁሉ የማንነት ተልእኮው ነውና፤ በሀገርና በወገን ተቆርቋሪነት የሚደረገው ሁለገብ ተልእኮ የእምነት፤ የዜግነት እዳ እንጂ የነገ ሹመት ማመቻቺያ ሊሆንም አይገባም። ሹመት ብቃትና እውቀት መለኪያው ሊሆንም ግድ ነው። ጥበብ፤ ትእግስትና ራእይም መመዘኛ መሆን ይገባቸዋል።

በወዳጅነት፤ በወንዜ ልጅነት፤ በአምቻና ጋብቻ፤ በፀረ ፍትህና ሰላም - በአጭሩ በፀረ ኢትዮጵያዊነት - ዘመነኞቹ ዘረኛ አምባገነኖች ሾመውና ሸልመው እንደላኳቸውና ሰሞኑንም እንደሚልኳቸው ባንዳ አምባሳደሮች - አይነት አሿሿም እኛ አንሾምም። ሹመት በእውቀትና በብቃት እንጂ በትውውቅና በባንዳነት አንሰጥም። ሹመት ሀገርን እና ወገንን ለማገልገያ እንጂ በሀገርና በወገን ለመገልገያ፤ ወይም ስልጣንን ለመጠበቂያ እንዲሆን አንሰጥም። ይህ መርሃችን ነው። መመሪያችን።

በመሆኑም ለዲበኩሉ የአምባሳደርነት ሹመት ይሰጥልን የሚለው ማመልከቻ ከላይ በጠቀስናቸው መስፈርቶች አኳያ ሚዛን የማይደፋ ሆኖ በማግኘታችን የሹመት ማመልከቻውን ይህ ጉባኤ ያልተቀበለው ሲሆን፤ ይኸው ውሳኔ ላመልካቾቹ በጥሁፍ እንዲገለጥላቸው ባንድ ድምጥ ወስነናል።

ለወዳጃችን ዲበ የጉባኤው ውሳኔ ሙሉ ቃል በኦፊሴል በመገናኛ ብዙሃን በኩል እንዲደርሰው ይሁን።

ሐምሌ 2002 ዓመተ ምህረት
የአራዳ ልጆች ጉባኤ
አራት ኪሎ ቤተመንግስት አፍንጫ ስር
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ